# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

## 12

★ በትጥቅ መብቃት

★ የወዝ አደሩ የሙያ ማኅበር አብዮታዊ ሚና

★ ወዝ አደሩ ይናገር

★ ዘር ቀለም ? ወይስ መደብ ? ?

ጥቅምት ፲፰—፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ለውይይት መነሻ

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቁጥር ፬ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# የፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር

፬ኛ ትምህርት—ከን. ዓ.

( ካለፈው የቀጠለ )

በፊውዳል ኅብረተሰብ ውስጥ ዋናው የምርት መሠረት እርሻ መሆኑ የታወቀ ነው ። የፊውዳልን ሥርዓተ ማኅበር ከሚከተሉት የምርት ኃይሎች ጋር ሲነፃጸሩ የፊውዳል ሥርዓት የምርት ኃይሎች ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ናቸው ። በዚሁ ልክ ደግሞ በምርት ግንኙነትም በኩል የዚህ ሥርዓት ዓይነተኛ የሆኑት በአራሽና በአሳራሽ መካከል ያሉት ግንኙነቶች በአሰቃቂ የብዝበዛ ሥርዓት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ነገር ግን የፊውዳል ሥርዓት ተጸንሶ የባርያ ሥርዓትን አፈራርሶና አድጎ ዓይነተኛ መልክን በያዘበት ወቅት በማንኛውም መስክ ቢሆን ቀድመውት ከነበሩት የጋርዮሽና የባርያ ሥርዓተ ማኅበራት መሆኑ አይካድም ፤ የተሻለ ሥርዓት ።

ፊውዳሊዝም ተወልዶ ፤ አንሰራርቶና በስብሶ በካፒታሊዝም በተተካበት በአውሮጳ የዚህ ሥርዓት መምጣት የምርት ኃይሎችን በጣም ሊያሳድጋቸው ችሎ ነበር ። ዋናው የኅብረተሰብ መሠረት እርሻ ቢሆንም በዚህ ዘመን በፈሳሽ ውሀና በአየር ኃይል የሚሠሩ ወፍጮዎች ፤ ከሥራ ላይ ዋሉ ፤ ታላላቅ መርከቦች ተሠርተው በውቅያኖሶች ላይ በመንሳፈፍ የንግድን ሥራ ማስፋፋት ጀመሩ ። የብረታ ብረት ፤ የወረቀት ፤ የጨርቃ ጨርቅ ፤ ሥራዎች ተስፋፉ ፤ የማተሚያ ቤቶች መፈልሰፍ ዕውቀትን ለማስፋፋት በጣም ረዳ ።

በዚህ ሁሉ ባለእጆች እየተራቀቁና ጠበብ ባሉ ሙያዎች እየሠለጠኑ ሄዱ ። ሥራ ወይም ምርት የሸቀጥ መልክ እየያዘ ሄደ ። ይህም ማለት ባለእጁ የሚሠራው ለራሱ የሚያስፈልገውን ያህል ብቻ ሳይሆን ገበያ ላይ አውጥቶ የሚሸጠውን ሆነ ይህም የንግድ ሙያንና የንግድን መስፋፋት አስከተለ ። ለዚህ ለመለዋወጥ ለመገበያየት ሥራ እንዲያመችና ባለእጆችም ፀጥታው በተጠበቀ አካባቢ ሠርተው በቅርብ ለነጋዴው እንዲያቀርቡ በታላላቅ ባለመሬቶችና መሳፍንት ቤተ መንግሥት በታላላቅ ደብሮችና አጥቂን ለመከላከል ታስበው በተሠሩት ምሽጎች አካባቢ መሰብሰብ ጀመሩ ። ይህም እንደገና ለከተሞች ማደግና ማንሰራራት ዓይነተኛ ምክንያት ሆነ ።

መለስ ብለን በዚህ ጊዜ የተፈጠረውን የምርት ግንኙነት የተመለከትን እንደሆነ የፊውዳል ሥርዓት የምርት መሣሪያው ማለት የመሬቱ ባለቤት ባለርስቱ ነበር ። ከላይ እንዳልነው በእርሻው ላይ ተሰማርቶ ከዚያው አካፍሎ ለመኖርና ለባለመሬት እንዲያድር የተገደደው ጢሰኛ ሙሉ በሙሉ አይሁን እንጂ የባለርስቱ ጥገኛ ነበር ። ለባለርስቱ በሳምንት የተወሰኑ ቀናት በጉልበቱ ማገልገል ነበረበት ።

ይህም ሆኖ በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ያለው የምርት ግንኙነት ከባርያ ሥርዓት ይሻላል ። ጢሰኛው እስከተወሰነም ደረጃ ድረስ ቢሆን ምርቱን ለማሳደግ ጠንክሮ ቢሠራ ድርሻው በመጠኑ ከፍ ይላል ። እንዲያውም በብዙ ቦታዎች ጢሰኞች የራሳቸው የሆነች በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ኩርማን መሬት ስለምትኖራቸው በባለርስቱ መሬት ላይ ለመሥራት ያለባቸውን ግዴታ ከፈጸሙ በኋላ እሷን በጥንቃቄና በትጋት በማረስ ኑሮዋቸውን ለማሸነፍ ይጥሩ ነበር ። ባለእጆችም ቢሆኑ የራሳቸው የሆኑ አነስተኛ መሣሪያዎች ስለሚኖራቸው እሱን ለማሻሻልና ምርትን ለማሳደግ ጥረት ማድረጋቸውን አልተውም ።

በዚህ መልክ በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ከባርነት ዘመን ይልቅ የእርሻ የባለእጅ የንግድ ሥራ እየተስፋፋ መሄዱ አያስደንቅም ። እንዲያውም

ቀስ በቀስ የፊውዳሉን ሥርዓት ቦርቡሮ ያዳከመውና ከዚያም እሱን ደምስሶ የካፒታሊስት ሥርዓትን መተካት የተቻለው እነዚህ የምርት ኃይሎች እያደጉ ሄደው አንድ የተወሰነ ደረጃ ሲደርሱ በይበልጥ ለማድረግ የግድ የፊውዳሉን ሥርዓት የምርት ግንኙነቶች በአዲስና በተሻለ የምርት ግንኙነት መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ።

ይህ የሆነው እንዴት ነው ? በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ የባለእጆች ሥራ እየተጠናከረ ሲሄድ ባለእጆች ከዕለት ጉርሳቸው አልፈው ለትርፍ መሥራት እንደጀመሩ እይተናል ። ይህ ደግሞ ባለእጁ ለገበያ እያለ የሚያሠራው ዕቃ «ሸቀጥ» ወይም «ማርቼንዳይስ» የመጭው የካፒታሊስት ሥርዓት ዓይነተኛ ምርት ነው ። ባለእጁ የገበያ ውጣ ውረዱን ትቶ በሸቀጡ ሥራ ላይ ብቻ ቢያተኩር ይበልጥ የሚያዋጣ በመሆኑ ገዝቶ ገበያ የማቅረቡንና ሸጦ የመጠቀሙን ሥራ በተለይ የነጋዴዎች ክፍል እየያዘው ሄደ ።

ባለእጆቹ በዚህ መልክ የሚዳብረውን ሥራቸውን መልክ ለማስያዝም በሥራ ዓይነት እየተፈላለጉ «ማኅበራትን» (ኮርፖራስዮን) በማቋቋም የሸማኔ ፤ የፋቂ ፤ የአናጢ . . . እየተባሉ ተደራጁ ። በዚህ መልክ የምርቱን ገበያ በሚያዋጣው ልክ ለመወሰን ፤ ዋጋውን ለመወሰን ፤ ማኅበርተኛ ያልሆነ ባለእጅ ሠርቶ ለገበያ እንዳያቀርብ ለማድረግ፤ ከሌላ አካባቢ ዕቃም እየመጣ የነሱን ገበያ እንዳያሰናክል ለመከላከል . . . ሲባል በመደራጀታቸው ምርቱ መልክ በያዘ ሁኔታ አደገ ። ነገር ግን እነዚህ ማኅበራት ወደኋላ ላይ አዳዲስ መሣሪያ ከሥራ ላይ እንዳይውል ፤ የባለእጆችም ሥራና ምሥጢር በመያዙ ዕውቀቱ እንዳይስፋፋ እየዘጉ ስለሄዱ አድኀሪ የሆነ ሚና ሳይጫወቱ አልቀሩም ።

የሆነ ሆኖ በዚህ የምርት ማደግ በመጠቀም የነጋዴዎች ክፍል ራሱን አዳበረ ። ገንዘቡም እንደገና ተስፋፍቶ «ገንዘብ ሸቀጥ ገንዘብ» የተባለው የካፒታሊስት ሥርዓት የትርፍ ማካበቻ ዘዴ ሥር መሰደድ ጀመረ ። ይህም ማለት ነጋዴው ሸቀጡን መጀመሪያ በ፲ ሳንቲም ይገዛው እንደሆነ በሚሸጥበት ጊዜ ደግሞ የዚያው ሸቀጥ ዋጋ ፲፭ ሳንቲም ሆኖ አምስት ሳንቲም ትርፍ ያገኝበታል ማለት ነው ። በዚህ መልክ ሀብት መሰብሰብ የጀመሩት ሰዎች ገንዘብ በማጠራቀም በመስፋፋት ላይ ባሉት ታዳጊ ባለእጆች ጥሬ ዕቃ ገዝተው በማቅረብም ሆነ ለነጋዴዎች የሸቀጥ መግዣ በአራጣ በማበደር ሀብት የሚያከማቹ አበዳሪዎች(ባንኮች)ተፈጠሩ።

ከዚህ በፊት ግን የባለእጆችን ምርት የሚያሳድጉና የካፒታሊዝምን መሠረት የሚያዳብሩ ለውጦች ተደረጉ ። እነዚህም በሁለት ደረጃ ሊከፈሉ ይችላሉ ። በመጀመሪያ ደረጃ ባለእጆች ሥራቸውን በማስተባበር ተሰብስበው በኅብረት ይሠሩ ነበር ። በዚህ ጊዜ በነዚህ ሰዎች መሀከል ምንም ዓይነት የሥራ ክፍያ አልነበረም ። በኋላ ግን «ማኒፋክቸር» የሚባለው የሥራ ዘዴ ተፈጠረ ። ይኸውም አሁንም ብዙ ሰዎች የሚሠሩ ቢሆንም ምርቱ በሥራ ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ነበር ።

በዚህ ሥራ የተሰማሩ ከበርቴዎች በዚህ መልክ ብዙ ጉልበት አንድ ቦታ ሰብስበው በሚያሠሩበት ጊዜ ካፒታሊዝምን ሕይወት የሚሰጠው ዓይነተኛ የሚያደርገው የብዝበዛ ዓይነት እየተጠቀሙ ነበር ። በነዚህ ፋብሪካዎች ለመሥራት የሚቀጠረው ሠራተኛ በቀን የተወሰነ ሰዓት ፋብሪካው ውስጥ ሊሠራ ይዋዋላል ። ለዚህ ሥራ የሚከፈለው ደመወዝ እሱና ቤተሰቡ በረኀብ እንዳያልቁ የሚከላከሉበትን ያህል ብቻ ነው ። ለዕለት ጉርሴ የምትሆነውን ብቻ ሠርቶ ቢያቆም በቀን ለምሳሌ ፫ ሰዓት ብቻ ይበቃዋል ። ግን ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ ሲሠራ ይህ ሠራተኛ «ለዕለት ጉርሱ የምትበቃኝን ሠርቻለሁ ላቁም» ሊል አይችልም ፤ መቀጠል አለበት ። በገባበት ውል መሠረት በቀን ፲ ሰዓት መሥራት አለበት ። ይህም ማለት ፋብሪካ ውስጥ ውሎ ከሚያመርተው ውስጥ የሰባት ሰዓት ልፋቱ ለሱ ሳይሆን ለአሠሪው ነው ማለት ነው ። ማርክስ ይህን አሠሪው በየዕለቱ ከሠራተኛው የሚያጋብሰውን ሀብት «ትርፍ ምርት» ወይም «ሰርፕለስ ቫልዩ» ብሎ ይጠራዋል ። የካፒታሊዝም መሠረትና የህልውና ምክንያትም ሆነ ድጋፍ ይህ ከሠራተኛው የሚቀማው «ትርፍ ምርት» ነው ማለት ነው ።

ነገር ግን ይህ የብዝበዛ ሥርዓት በፊውዳሊዝም አብራክ ተጠነሰሰ እንጂ አድጐ የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆን የግድ የፊውዳል ሥርዓት ተደምስሶ መውደቅ ነበረበት ።

ከበርቴው እንደዚህ የሚያዋጣውን የብዝበዛ ሥርዓት ማስፋፋት የሚቻለው በዚያው ልክ የሚበዘብዝ ጉልበት ተገኝቶ «ትርፍ ምርት» ሲያድግ ነው ። ስለዚህ ትርፍ ለማጋበስ ነፃ የሆነ ጉልበት ያስፈልገዋል ። «ነፃ የሆነ» የምንለው ከሁለት አንፃር ነው ። አንደኛ ከባላባት ጥገኝነት ነፃ ሆኖ ጉልበቱን ለመሸጥ <u>የሚችል</u> ሰው ሁለተኛ ሙልጩን ወጥቶ በዚህ መልክ ከሀብትም ከንብረት « ነፃ » ሆኖ ኑሮውን ለማሸነፍ ጉልበቱን ለመሸጥ <u>የሚገደድ</u> ሰው ማለት ነው ።

የባለርስቱ መደብ ግን ጢሰኞቹ ከጥገኝነት ቢወጡ ከነሱ ጉልበት የሚያገኘው ምርት ስለሚቀርበት ገበሬዎች ወደከተማ እንዳይሄዱ ይፍጨረጨር ነበር ። በዚህ ልክ ደግሞ ባለርስት እያሳደደ የሚያስቸግራቸውን የኮበለሉ ጢሰኞች የከተማ ከበርቴዎችና ነጋዴዎች ይከላከሉላቸዋል ። ከባላባቱ ቁጥጥር ሥር ከወጣ በኋላ አንድ ጢሰኛ ምንም ሀብት ስለሌለው ያለው ምርጫ ወይ በረኀብ ማለቅ ወይ ደግሞ የምርት መሣሪያዎች ላላቸው ከበርቴዎች ተቀጥሮ ጉልበቱን እየሸጠ መኖር ከተማ ገብቶ ያለጉልበቱ ያለወዙ ምንም መተዳደሪያ ስለሌለው ነው ወዝአደር የምንለው ።

በዚህ መልክ ከተማ እየመጣ ጉልበቱን ለከበርቴ የሚያቀርበው ኮብላይ ጢሰኛ ብቻ አልነበረም ። የፋብሪካ ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድና ካፒታሊዝም በገጠር ሲስፋፋ ብዙ ጢሰኞች ከመሬታቸው እየተነቀሉ ሥራና እንጀራ ፍለጋ ወደከተማ እንዲጐርፉ ተገደዋል ። ለዚህ የሚጠቀሰው የታወቀው ምሳሌ የእንግሊዝ አገር ካፒታሊዝም አስተዳደግ ነው ።

የጨርቃ ጨርቅ ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ ፋብሪካዎች ብዙ ሱፍ አስፈልጓቸው ነበር ። ስለዚህ በግ ማርባት እጅግ የሚያዋጣ ንግድ ሆነ ። ይህንን የተመለከቱ ታላላቅ ባለርስቶች በግ እያረቡ ለመሸጥ በማሰብ ለግጦሽ መሬት ሲሉ ጢሰኞቻቸውን ያለአንዳች ርኅራኄ በመንቀልና ሰፋፊ የግጦሽ መሬቶችን በማጽዳትም የበግ ማርቢያ አደረጓቸው ። አንድ የጊዜው የእንግሊዝ ጸሐፊ እንዳለው «በጉ ሰው በላ» ብዙ የቀድሞ ጢሰኞች ከነቤተሰቦቻቸው ከረኀብ ለመዳን ወደ ከተማ እየፈሰሱለት ባለፋብሪካው ከበርቴ ርካሽ ጉልበት መዛቅ ጀመረ ። በእንግሊዝ አገር የካፒታሊዝም ዕድገት ታሪክ በዚህ መልክ የተጋበሰው ትርፍ ለካፒታል መዳበር ታላቅ ምክንያት ሆንዋል ።

ይህ በሆነ በሦስት መቶ ዓመቱ የኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም እንደዚሁ እየበሰበሰ ገና አፍላ ላይ የሚገኘው የካፒታሊስት አዲስ ጉልበት በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ ቦለቄ ፤ ጥጥ ፤ በቆሎ ... በዘመናዊ መልክ ለማምረት ጢሰኞችን እንዴት ቤታቸውን በላያቸው ላይ እያፈረሱና እየጠራረጉ ምርቱን ለማሳደግ እንደሞከረ ገና የምንረሳው አይደለም ።

በዚህ ላይ ደግሞ ከ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ይኸው የምርት ኃይሎችም የሥራ መስፋፋት ባስገኘው ጥበብ ታላላቅ መርከቦች መሥራት በመቻሉ አዳዲስ አህጉራትና ከዚህ በፊት ያልተደረሰባቸው ብዙ ግዛቶች በቅኝ ግዛት መልክ መያዝ ቻሉ ። ከነዚህ ከቅኝ ግዛቶች የሚመጣው የማዕድን ሀብት ፤ ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃ ፤ ወደነዚህም የሚወስደው ሸቀጥ በጠቅላላው በምዕራብ አውሮፓ የካፒታል ማከማቸቱን ተግባር እጅግ የተቃና አደረገው ። ኢኮኖሚው ከዚህ በፊት ጨርሶ ባልታየና ባልተሰማ ሁኔታ ዳበረ ። በዚሁ ሁሉ መሀል እንግዲህ የዚህ በመወለድ ላይ ያለ አዲስ ሥርዓት ሁለት ተቀናቃኝና ተፃራሪ መደቦች ማለትም

ከበርቴውና ወዝአደሩ በየበኩላቸው እየተጠናከሩ ሄዱ ።

ይህ ሁሉ በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ የተደረገው መለዋወጥ በፖለቲካውና በአይዲዮሎጂ በኩል እንደሚጠበቀው ሁሉ ከፍተኛ ለውጥን አስገኘ ። በፖለቲካ የሄድን እንደሆነ ከላይ ባጭሩ እንደጠቀስነው የተከታተልነው የፊውዳል አገዛዝ ለፀጥታም ሆነ ለንግድ (በያለበት እያንዳንዱ ፊውዳል በግዛቱ የሚያልፈውን ሁሉ ካልቀረጥሁ እያለ ያስቸግራል) አልመች በማለቱ የከተማ ነጋዴዎችና ከበርቴዎች በያለበት አለሁ አለሁ የሚለውን የመ ንደር አምባገነን ባላባት ሁሉ ጭጭ አድርጐ በአንድ በተጠቃለለ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ሥር የሚያስተዳድር ጠንካራና ማእከላዊ አገዛዝ እንዲመጣ ታገሉ ። ይህም ከሆነ በኋላ በዚህ በተጠቃለለ ግዛት ውስጥ የሚገኘውን ገበያ ሁሉ ከውጭ ሌላ ተወዳዳሪ ሳይሻማቸው ተጠብቆ ቢያዝላቸው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በከበርቴ መደብ ግንባር ቀደምነት «የብሔር ግዛት» (ነሽን ስቴትስ) የሚባለው ከካፒታሊዝም ጋር አብሮ እያደገ መጣ ።

በአይዲዮሎጂ በኩል የሄድን እንደሆነ በዚሁ በመወለድና በማደግ ላይ ባለው ከበርቴ አማካይነት በመበስበስ ላይ ያለውን የፊውዳል ርእዮተ ዓለም በየአቅጣጫው እየተቋቋመ ምርትን፣ ጥናትን፣ የዕውቀትን መስፋፋት ፣ ሳይንስን ፣ ቴክኖሎጂን የሚያግዝ አስተሳሰብ ሁሉ ከፍተኛ ግምት የሚሰጥበት ወቅት መጣ ። በተለይ ይህን ተሐድሶ (ረሳንስ) የሚሉትን በ፲፬ኛውና በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ (በተለይም በጣልያን) መስፋፋት የጀመረውን ንቅናቄ ታዳጊው ካፒታሊዝም ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ተቀበለው ።

ቀደም በቤተ ክህነት ሁሉን አዋቂነት ላይ ተመስርቶ የነበረው እምነት ሁሉ በተጨባጭ ማስረጃዎች በታዳጊው ሳይንስ እየተሻረ ሄደ ። በራስ በሃይማኖት እንኳን ብንሄድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የለውጡን ሞገድ መቋቋም አልቻለም ። እርግጥ ነው ታዳጊው ከበርቴ አብሮት ያለውን ተበዝባዥ ስለሚፈራ ሃይማኖት ጨርሶ ይጥፋ የሚልበት ደረጃ አልደረሰም ። ነገር ግን የጊዜውን ሃይማኖት ለታዳጊው ካፒታሊዝም እንዲያመች ሆኖ መቀየር አስፈላጊ በመሆኑ « ለባላባቱ ገዥ መደብ ሙሉ በሙሉ ታዘዙ ይል የነበረው ሃይማኖት በተለይ ከተማ እየገባ ዕውቀቱን እያዳበረ በሄደው ጢሰኛ ዘንድ ተቀባይነቱ በመቀነሱ የተሻለና ይበልጥ የተራቀቀ ከጊዜው ጋር የማይራመድ ሃይማኖት አይኖርም» በሚል ንቅናቄ አሳቦ ስለመጣ ፕሮቴስታንቲዝም የከበርቴውና የካፒታሊዝም ዓይነተኛ ሃይማኖት ሆኖ መጣ ።

ይህ በሃይማኖት አስመስሎ የቤተ ክህነትን ፈላጭ ቆራጭነት የሚቃወም ሃይማኖት በጊዜው ቤተ ክህነትም አንደኛ ዋና ባላባት ነበረችና ጢሰኛውን መቀስቀስ ቻለ ። በሌላ በኩል ደግሞ የግል ጥረትን ፣ መፍጨርጨርን፣ ግለሰበኝነትን ስለሚያነግስ ለካፒታሊስት ዕድገት አመች በመሆኑ ከበርቴው አቀፈው ።

እንግዲህ በዚህ ሁሉ በፊውዳሊዝም መበስብስና በካፒታሊዝም ዕድገት ለማደግም መፍጨርጨር የተነሣ በያለበት በከበርቴው መደብ የሚመሩ አመጾች እየተደጋገሙ በመነሳታቸው በአውሮፓ ያረጀው የፊውዳል ሥርዓት መፈራረስ ጀመረ ። «ታላቁ የገበሬዎች ጦርነት » በሚባል ስም የታወቀው የጀርመን ገበሬዎች አመጽ ከ፲፭፻፳፬—፳፭ ተደርጐ ለጊዜው በባላባቶች ኃይል የተደመሰሰ የመጀመሪያው የከበርቴ አብዮት ሙከራ ተደርጐ በነዚሁ ሐሳቦችና ዓላማዎች ላይ በተጨማሪ የስፔን የበላይነት የተጫናቸውና ያፈነው የኔዘርላንድስ ከበርቴ ግን በትግሉ ጸንቶ በ፲፮፻፱ ዓ. ም. የመጀመሪያውን የተሳካ የከበርቴ አብዮት አከናወኑ ። ከዚያም በማከታተል እንግሊዞች በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የእንግሊዝ ከበርቴ አብዮት ፣ አደረጉ ። ፲፯፻፹፱ ደግሞ በዓለም ታሪክ ከፍተኛ ቦታ የያዘው ታላቁ የፈረንሳይ ከበርቴ አብዮት ተደርጐ ለመላ ዓለም አዲስ የከበርቴ የበላይነት ዘመን ተከፈተ ። ይኸውም ካፒታሊዝም ወደተባለው ሥርዓት ማኅበር ያመጣናል ። (ይቀጥላል)